ለጀርመን ድምፅ አማርኛ ፕሮግራም አዘጋጅ

የዘመናት አድማጫችሁ ነኝ ፡፡

ባለፈው ጥር 9 ቀን 2007 ዝግጅታችሁ ላይ የጉርሱሙ ነዋሪ ተገኔ ባይሣ ያለፈው የኢትዮጵያ ታሪክ የፉክክር፣ የመጋደልና የደም ማፍሰስ ታሪክ እንደነበረ አውስተው ለምሣሌ ያህል የአፄ ቴዎድሮስንና የአፄ ምኒልክን ዘመናት ጠቅሰዋል ፡፡ እውነት ነው፣ ደም ፈስሷል፣ ወገን እርስ በእርሱ ተጋድሏል፡፡ የወንድሜ የተገኔ ችግር ሁሉንም ጦርነት በጅምላ አንድ ዓይነት አድርጎ የመመልከትና ከዓለም ታሪክም፣ በተለይ የአውሮፓንና የአሜሪካን ታሪክ ቢያውቁ ኖሮ በአገራችን ልዩ ታምር ባልጠበቁ ነበር፡፡

አፄ ቴዎድሮስ በመሣፍንት የተከፋፈለችውን ኢትጵያችንን አንድ ለማድረግ በየቀበሌው ሲንከራተቱ፣ በአውሮጳም እንዲሁ በመንደር ገዢዎች የተከፋፈለችውን ጣሊያንን አንድ ለማድረግ በሳርዲኒያው መሥፍንና በጋሪባልዲ የተመራ የቀይ ሸሚዝ ጦር ጣሊያንን በጦር ሃይል ያሰባስብ ነበር፡፡ የአያሌ ንዑሳን መንግስታት አገር በነበረችው ጀርመንም፣ ሀያሉ የፕራሺያ መሪ፣ ቢስማርክ፣ ከፍተኛ የጦር መሣሪያ ፋብሪካ ገንብቶ፣ እሺ ያሉትን ንዑሳን የጀርመን መንግስታት በሰላም ፣ እንዋጋለን ያሉትን ደግሞ በጦር አንበርክኮ የዛሬዋን ሃያል ጀርመን የመሰረተው በዚያው በአፄ ቴዎድሮስ ዘመን ነበር ፡፡ እነዚያም ጣሊያንንና ጀርመንን ያሰባሰቡ መሪዎች ዛሬም በየዜጎቻቸው እጅግ የተከበሩ ናቸው። የአሜሪካውም አብርሃም ሊንከልንም፣ የአሜሪካ የአንድነት አባት፣ እንዲሁ በዚያው ዘመን አካባቢ፣በአሜሪካ ደም እንደ ጎርፍ ፈስሶ የአሜሪካን አንድነት በማስጠበቁ፣ ዛሬ በሁሉም አሜሪካውያን ዘንድ የተከበረ መሪ ነው፣ ግዙፍ ሀውልትም በዋና ከተማው ጭምር ቆሞለታል ፡፡

እዚህ ኢትዮጵያ ግን አፄ ቲዎድሮስና አፄ ምኒልክ በውለታ-ቢሶችና ባንዳዎች ዛሬም ይወቀሳሉ ፡፡ ይህ ከጋራ ዘላቂ ጥቅም ይልቅ የግል ጥቅም ቅድሚያ የመስጠት አባዜ፣ ውዳቂ አስተዳደርና ከፍተኛ ችጋር በአገራችን እንዲንሰራፋና፣ በሁለት ዲጅት አደገች በተባለላት አገራችን ድህነት፣ ረሃብና ስደት ቋሚ መታወቂያችን እንዲሆኑን ያደረገ በሽታ ነው ፡፡ ዛሬ፣ የአማራ-ትግሬ፣ የአማራ-ኦሮሞ፣ የኦሮሞ-ኦጋዴኒ የወሰን ክለላ ትርምስ፣ የመንደር ዕውቅናው ግብግብ፣ የኑሮ ውድነት አለመገታት፣ የብር መቆሚያ-የለሽ ግሽበትና የመንግስቱ የኢኮኖሚ ፖሊሲ ቋሚ ድህነት፣ ኋላ-ቀር እርሻችን በ24 ዓመት ባለመቀየሩ በሌልኒኖ እየተሳበበ ድርቅ፣ ረሃብና ችጋር መስፈን፣ ሕግና ሥርዓት የማያውቅ የወያኔ ጥሬ ታጋይ የሕግ ተርጓሚውን (Judiciary) ዘርፍ የኪራይ ስብሳቢዎች መሣሪያ ማድረግ፣ ከ30 በላይ ዩኒቬርሲቲ ገንብቶ የመሃይም መፈልፈያ ማድረግ፣ ከኤርትራ ወንድሞቻችን ጋር በግል ጥቅምና ሥልጣን-ወዳድነት ግጭት የተፈጠረውን መቃቃር መፍቻ አቅምና ዕውቀት ማጣትና አገራዊ ጥቅሞቻችንንና የቀይ ባሕርን ለባዕድ መንግሥታት አሳልፎ በመስጠት ሉዓላዊነታችንን ለከፋ አደጋ ማጋለጥ፣ እንዲሁም ዳር ድንበራችንን እየሸረሸሩ መሬታችንን አሳልፎ ለባዕድ መቸርቸር የደካማ ፖለቲካና የውዳቂ ኢኮኖሚ አመራር መገለጫዎች ናቸው ፡፡

የዛሬውን የከፋ የመንግሥት አስተዳደር መለወጫው ዘዴ አስመሳይ ሹም-ሽር አድርጎ፣ ለመንግሥት መበስበስ ዋና ተጠያቂ የሆኑትን ምርጥ ኪራይ ሰብሳቢዎችና ሙሰኞች ጠቅላይ ሚኒስትር ቢሮ በአማካሪነት ማከማቸትና በጠቅላይ ሚንስትሩ ስም በሶስቱም የመንግሥት ዘርፎች ኪራይ ስብሳቢዎችን አድራጊ-ፈጣሪ ማድረግ ሳይሆን፣ በ<u>**እውነተኛ የመድበለ-ፓርቲ ሥርዓት ፍጹም ነፃ ምርጫ (እንደ ቤኒን፣ ጋና፣ ሴኔጋል፣ ታንዛኒያ፣ ወዘተ) ማድረግ ብቻ ነው**</u> ፡፡ በኢሐአዴግ ሊቀ መንበር የተመለመለ የምርጫ ቦርድና በኢሕአዴግ ብቻ የተዘጋጀ የምርጫ ሕግና የአፈጻጸም ሥርዓት ውጤት ያደራጃቸውን <u>**ኢህአዴግንና ሙሰኞችን ባለሥልጣኖቹን ማገልገል ብቻ ነው**</u> ፡፡ ባለፉት 24 ዓመታት የሆነው ይህ ነው ፡፡ የአገራችንም ችግር እያደገ የሄደውም በዚህ በሕዝብ ተጠያቂ ያልሆነ ኪራይ-ሰብሳቢ ቡድን ፈላጭ-ቆራጭ መሆን ምክንያት ነው ፡፡ ዛሬ፣ ጠቅላይ ሚኒስትር 3 ምርጫዎች አሏቸው፡- አንዱ ሹሞቻቸውን በንጹህና ብቁ ባለሙያዎች መተካትና ለነፃና ታሪካዊ ምርጫ በድፍረት መዘጋጀት ነው ፤ 2ኛው ያላቸውን የበሰበሰ መንግሥት ይዘው የአገራችንን የገደል መግቢያና የውርደት ጉዞ መቀጠል ነው ፤ 3ኛው ወደ ንጹሁ የአስተማሪነት ሥራቸው መመለስ ነው ፡፡

ነፃ ምርጫ እስካልተደረገ ድረስ፣ የመንግሥት መበስበስና የሕዝብ መታፈን ይቀጥላል፣ የታፈነ ሕዝብም አንድ ቀን አብሮ መነሳቱ አይቀርምና፣ ያን ጊዜ የጃንሆይና የደርግ መንግሥት ሹማምንት ዕጣ ፈንታ አይቀሬ ነው ፡፡ ሁልጊዜ ሕዝብን በወታደር እናፍናለን ብሎ በኢትዮጵያ ወታደር መተማመን፣ ራስን ለውድቀት ማመቻቸት ነው ፡፡ በበኩሌ በሃይል የሚመጣ ለውጥ አልደግፍም፡፡ ከነፍጥ-ነካሾች ደርግና ከኢሕአዴግ እንዳየነው፣ ኢትዮጵያ አንደ <u>**ቤኒን፣ ጋና፣ ሴኔጋልና ታንዛኒያ ያለ የተረጋጋ ዲሞክራሲያዊ መንግሥትና አመራር**</u> አላገኘችም፡፡ ዛሬም የኦጋዴን ነፃ አውጪ ግንባር፣ የኦነግ፣ የግንቦት 7፣ እና የኤርትራ ጉዳይ መፍትሄ ባለማገኘታቸው ምንጊዜም ታሪካዊ ጠላቶቻችን ኢትዮጵያን <u>**ለማተራመስ (የ ELF ን የካይሮ ምሥረታና የኤርትራን ማስገንጠል ታሪክ ልብ ይሏል፡፡) የሚያስችላቸው ቀዳዳ**</u> ከባለጉዳዮች ጋር በመመካከር አልተዘጋም ፡፡ የምመኘው እንደ <u>**ጋና፣ ቤኒንና ሴኔጋል**</u> ለውጥ በሰከነ ምርጫ እንዲመጣና ኢሕአዴግም ራሱን አሻሽሎና ሀቀኛ የሕዝብ አጋር ሆኖ፣ ነፃ ድምጽ የሚያገኝበት ዘመን ላይ እንድንደርስ ነው ፡፡ የአዲስ አበባ <u>**የአፍሪቃም መዲናነት ስብከት ሀቀኛ ትርጉም የሚኖረው ያኔ ብቻ ነው ፡፡**</u>

መንግሥታችን ሕንጻዎችንና መንገዶችን በስፋት እንደነገሩ ቢሠራም፣ በ24 ዓመት አገዛዙ ከሙሰኞች፣ ከረሃብ፣ ከችጋርና ከስደት ነፃ ሆነን፣ የሁሉም ዜጎች መብት እኩል ተከብሮ፣ የተረጋጋ ዲሞክራሲያዊ ሥርዓት ሊገነባ አልቻለም፡፡ ዛሬም እንደ ደርግ የሕዝብን ሀብት አግበስብሶ ወስዶ፣ መንግሥታችን ከዓለም መንግሥታት 1.4 ቢሊዮን ዶላር <u>**እንዲረጠብ**</u> <u>**ያለሀፍረት ይወተውታል**</u>፣ ይህን ገንዘብ ሳያገኝ ቀርቶ በአገራችን ክፍተኛ ችግር ቢከሰት የእኛ መንግሥት ተጠያቂ አይደለሁም ይላል፡፡ ከዚህ መንግሥት ሌላ ማን ተጠያቂ ይሁን ትላላችሁ ?

እባካችሁ የሚሰማ ቢገኝ መልዕክቱን አስተላልፉልኝ፡፡ስሜን አታሰሙ እባካችሁ፡፡